**ያቁሙ**

# የአየር ወለድ በሽታዎች ቅድመ ጥንቃቄዎች

**ጎብኚዎች** ከመግባታቸው በፊት ከነርስ ጋር ይገናኛሉ።

## የተከለከሉ ጉብኝቶች

## ከመግባትዎ በፊት፡



**እጅዎን ይታጠቡ**




**National Institute for Occupational Safety and Health (NIOSH,ብሔራዊ የሙያ ደህንነት እና ጤና ተቋም) መተንፈሻ ይጠቀሙ**
**(N95/PAPR/CAPR)**

## ሌላ መስፈርቶች፡



**ለአየር ወለድ-በሽታ መከላከያ ክፍል ከፍተኛ ቅድሚያ መስጠት። ካለ፣ በሮ እንደተዘጋ ያቆዩ።**



**ለታካሚ ብቻ የተፈቀዱ ወይም ልጣሉ የሚችሉ መገልገያዎችን ይጠቀሙ። የጋራ መገልገያዎችን በፀረ ተባይ ያጽዱ።**

ከበር ውጪ ያሳዩ። ክፍሉ ንጽህ የአየር ዝውውር እንድያገኝ ሲባል በሩ ለአንድ ሰዓት ዝግ ነው የሚል ምልክት ለጥፈው ይውጡ።
ክፍሉ ሙሉ በሙሉ ከጸዳ በኋላ የ Environmental Services (አከባቢ አገልግሎት) ሠራተኞች ምልክቱን ያነሳሉ።

*ቅድሙ ጥንቃቄ ከተቋረጠና ክፍሉ ከጸዳ በኋላ ምልክቱ Environmental Services (በአከባቢ አገልግሎት) ሠራተኞች እንዲነሳ ይደረጋል።*

*የአየር ወለድ በሽታዎች ቅድመ ጥንቃቄዎች*

**ሁኔታዎች ላይ በመመስረት የተከለከሉ ጉብኚቶች: ሠራተኞች በመገልገያ ፖሊሲ መሠረት ለጎብኚዎች ተገብውን ትምህርትና የግል መከላከያ መሣሪያዎች(PPE) የግድ መስጠት አለባቸው።**

*የግል መከላከያ መሣሪያዎች (PPE)*

***በመደበኛ ቅድመ ጥንቃቄዎች መሠረት ለሎች የግል መከላከያ መሣሪያውች በተጨማሪ፣ በመጀመሪያ ገጽ ላይ የተዘረዘሩትን የግል መከላከያ መሣሪያዎች በመያዝ፣ የሚከተሉት ቅደም ተከተሎች ለሁሉም የግል መከላከያ መሣሪያዎች ማሳያዎች ናቸው።***

| *የግል መከላከያ መሣሪያዎች (ልገሳ) ማድረግ።* | *የግል መከላከያ መሣሪያዎች ማውለቅ* |
|---|---|
| 1. የእጅ ንፅህናን ያከናውኑ<br>2. መከላከያ ጋዎን፣ አስተማማኝ የሆነ ጥምጣም/ከረባት ያድርጉ<br>3. መተንፈሻ ወይም የፊት ጭምብል ማድረግ፣ ተስማሚና በትክክል መግጠማቸውን ማረጋገጥ።<br>4. የፊት መሸፈኛ ወይም መነጽር ይጠቀሙ<br>5. ጓንቶችን ያድርጉ | **የተጠቀማችሁት CAPR/PAPR ከሆነ፣ በትክክል ለማውለቅ የአምራች አጠቃቀም መመሪያዎችን ይከተሉ።**<br>1. ከታካሚ ክፍል ውስጥ ከሆናችሁ፣ እጅን በማይበክል መልኩ ጓንቶችን ያውልቁ።<br>2. ጋዎን ያውልቁ - ከረባት/ጥምጣም ይፍቱ፣ ሊጣሉ ለሚችሉ ጋዎኖች ማሰሪያ የሚውል ከሆነ ከረባቱን ይቁረጡ። እያንዳንዱን ክንድ ለማስወገድ አንድ ትከሻን በአንድ ጊዜ በመያዝ ያስወግዱ። ካወለቃችሁ በኃላ በመጠቅለል ትክክለኛ ማስቀመጫ ውስጥ ያስቀምጡ። አሁን ከክፍሉ መውጣት ትችላላችሁ።<br>3. ስትወጡ፣ የእጅዎን ንጽሕና (የሚታይ ቆሻሻ፣ የሰገራ ንክኪ ወይም ከቅድመ-ጥንቃቄ መጓደል ንክኪ አጋጥምዎት ከሆነ፣ ሳሙና ውኃ ይጥቀሙ) ያከናውኑ።<br>4. የፊት መሸፈኛ/መነጽር ያውልቁ - ተበክሎ ሊሆን ስለሚችል የዓይን መከላከያ መጀመሪያ ክፍል አይንኩ።<br>5. መተንፈሻ/የፊት ጭምብል በትክክል በመያዝ ያውልቁ - ተበክሎ ሊሆን ስለምችል የፊት ለፊት ክፍል ከመንካት በመቆጠብ እንዳይበክል አድርገው ተገቢ በሆነ መልኩ ይጣሉ።<br>6. የእጅዎን ንፅህና ደጋግመውይጠብቁ። |

**እንደ ሁኔታዎች ለመጠቀም: (የተቋሙ ፖሊሲ ይመልከቱ)**

- በኢንፌክሽን መከላከል በተሰጠ መመርያ መሠረት እየተከሰቱ ያሉ በሽታዎች።
- የሳንባ ቲቢ

**የታካሚ ምደባ**

- ታካሚን በግል ክፍል ውስጥ ይመድቡ። በይበልጥ የአየር ወለድ በሽታ መከላከያ ክፍል (AIIR) ይመረጣል። የማይገኝ ከሆነ፣ የተቋሙን መመሪያ ይከተሉ።

**ምግቦችና ዕቃዎች**

- ልዩ ቅድመ ጥንቃቄዎች የሉም። የማዕድ ቤት ዕቃዎች ዕቃ ማጠቢያ ውስጥ ይጠቡ።

**የቆሻሻ እና የአልጋ ልብስ ንጽሕና አጠባበቅ**

- አልጋ ልብስ ከታካሚ ክፍል ውስጥ ያስቀምጡ ከመጠን በላይ ንክኪና አልጋ ልብስ ማራገፍን ያስወግዱ። ለባዮአዛርድ ቆሻሻ፣ ምድብ ቢ የህክምና ቆሻሻ መመሪያዎችን ይከተሉ።

**ክፍልን ማጽዳት**

- ታካሚው ከወጣ በኃላ ለAIIRs በተቋሙ መመሪያ መሠረት ክፍሉ ተገቢ የሆነ የአየር ዝውውር እንድኖረው በሩን ዘግተው ያቆዩ።
- ከአንድ ሰዓት በኃላ በሆስፒታሉ አሠራር መሠረት የግል መጋረጃ ቅየራና መደበኛ የጽዳት ሂዴቶች ይካሄዳሉ።

**መሣሪያና አቅርቦቶች**

- ከታካሚ ክፍል ውስጥ ያሉ አስፈላጊ የሆኑ መሣሪያና አቅርቦቶችን ብቻ ይጠቀሙ።
- ለታካሚ ብቻ የተፈቀዱ ወይም ልጣሉ የሚችሉ መገልገያዎችን ይጠቀሙ።
- በተቋሙ ፖሊሲ መሠረት ድጋሚ የሚያገለግሉ መሣሪያ/የታካሚ ክፍል ፀር-ተባይ መርጨትና ማጽዳት።

**ትራንስፖርት**

- የታካሚውን የመውጫ ቅድመ ጥንቃቄ ሁኔታ ለተቀባይ ክፍል ማሳወቅ።
- ታካሚው እጁን መታጠብ አለበት። ታካሚው <u>የቀዶ ጥገና ጭምብል መጠቀም አለበት</u>።
- አጓጓዥ ከታካሚው ክፍል ከመውጣቱ በፊት እጁን መታጠብና የግል መከላከያ መሣሪያ ያወጣል። በመጓጓዣ ጊዜ ቀጥተኛ ግንኙነት የሚጠበቅ ከሆነ ተገቢውን PPE ይልበሱ።
- የትራንስፖርት መኪናን ፀረ-ተባይ መርጨትና ማጽዳት።

*በተቋሙ ፖሊሲ መሠረት ቅድሙ ጥንቃቄ ያቋርጡ፡*

*ቅድሙ ጥንቃቄ ከተቋረጠና ክፍሉ ከጸዳ በኋላ ምልክቱ Environmental Services (በአከባቢ አገልግሎት) ሠራተኞች እንዲነሳ ይደረጋል።*

**420-585 April 2024 Amharic**

ይህን ሰነድ በሌላ ቅርጸት ለማግኘት፣ ወደ 1-800-525-0127 ይደውሉ። መስማት የተሳናቸው ወይም መስማት የሚቸግራቸው ደንበኞች ወደ 711 (Washington Relay) መደወል ወይም ወደ doh.information@doh.wa.gov ኢሜይል ማድረግ ይችላሉ።

Washington State Hospital Association

7/30/2024

Washington State Department of HEALTH